# ጋዜጣዊ መግለጫ

አሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ
2014/22

ለተጨማሪ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
ድረ-ገጽ - http://ethiopia.usembassy.gov

---

## የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ የዘመናዊ ግብርና አገልግሎት መርሃ ግብር በሻሸመኔ የግብርና አገልግሎት ማዕከል ከፈተ

*የሻሸመኔው የዘመናዊ ግብርና አገልግሎት በኢትዮጵያዊያን ባለቤትነት ከሚተዳደሩና በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ የግብርና ድርጅቶች ስድስተኛው ነው*

***ሻሸመኔ፣ ኦሮሚያ ክልል፣ ኢትዮጵያ፣ ሰኔ 05 ቀን 2006 ዓ.ም.፤*** የአሜሪካ መንግስት በዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲው (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) የዘመናዊ ግብርና አገልግሎት መርሃ ግብር በኩል የሻሸመኔ ግብርና አገልግሎት ማዕከልን በዛሬው ዕለት መርቆ ከፈተ፡፡ ማዕከሉ በኦሮሚያ ክልል ከተቋቋሙ ተመሳሳይ ማዕከላት ስድስተኛው ሲሆን ፣ሌሎቹ በአምቦ፣ ቢሾፍቱ፣ ዶዶላ፣ ፍቼ እና ነቀምት ይገኛሉ፡፡ የግብርና አገልግሎት ማዕከላቱ ኢትዮጵውያን ባለ አነስተኛ ይዞታ አርሶአደሮችን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ የአመራረት ዘይቤ በማላቀቅ ወደ ዘመናዊ ግብርና ማሸጋገር የሚያስችሉ እንደ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የአረም መከላከያ፣ የእንስሳት መድሃኒት፣ መረ ጃ እና የገበያ ትስስርን የመሳሰሉ በርካታ ግብዓቶችን ያቀርባሉ፡፡

በሲቲዝንስ ኔትወርክ ፎር ፎሬይን አፌይርስ (ሲ ኤን ኤፍ ኤ) የሚተገበረው ይህ መርሃ ግብር፤ በገጠር የሚገኙ ስራ ፈጣሪ ወንዶችና ሴቶች፤ በኢትዮጵያውያን ባለቤትነት የሚመሩ የግብርና አቅርቦትና አገልግሎት የችርቻሮ ማዕከላት ማቋቋም እንዲችሉ የገንዘብ ድጋፍ እና ስልጠና ይሰጣል፡፡ እነዚህ በግል ይዞታነት የሚተዳደሩ የንግድ ድርጅቶች በኢትዮጵያ እና በመላው አፍሪካ በግብርና አገልግሎት የችርቻሮ አቅርቦት ዘርፍ ሞዴል ሆነው ያገለግላሉ፡፡

በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተገኙት በኢትዮጵያ የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ሚሽን ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር፤ “ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ  እና ሲ ኤን ኤፍ ኤ  ጥራት ያላቸው ግብአቶችን፣ አስተማማኝ ምርቶችን እንዲሁም የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች ምርታቸውን እና ገቢያቸውን እንዲጨምሩ እገዛ የሚደርጉት እነዚህን ማዕከላት በማቋቋማቸው ደስታ ይሰማቸዋል፡፡  የሻሸመኔው ማዕከል በኦሮሚያ ከተቋቋሙ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ስድስተኛው ሲሆን፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአካባቢው ለሚገኙ አርሶአደሮች ድጋፍ የሚሰጥ ማዕከል እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን፡፡” ብለዋል፡፡

በተገቢው የውድድር ሂደት በማለፍ የተመረጡት ስድስቱ በኢትዮጵውያን ባለቤትነት የሚመሩ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው 40,000 የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ የተደረገላቸው ሲሆን፤ እነዚህ ባለሃብቶች ቢያንስ ከዚህ ተማጣጣኝ የሆነ የራሳቸውን ገንዘብ ለድርጅቱ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡ይህም የማዕከሉ ባለቤት በድርጅቱ ላይ የራሱን መዋዕለ ነዋይ ጭምር ማፍሰሱን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

የሻሸመኔ ግብርና አገልግሎት ማዕከል ባለቤት እና አንቀሳቃሽ የሆኑት አዳነች ዘውዴ “በዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ያልተቆጠበ ጥረት እና በተደረገልን ድጋፍ ግብዓቶችን በቀጥታ ከውጭ አገር ማስመጣት ስለምንችል እና በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ አገናኞችን ስለሚያስቀር ምርቶችን በአነስተኛ ዋጋ

ማቅረብ እንችላለን፡፡ ይህ ትልቅ ስኬት በሻሸመኔ ለሚገኙ ባለአነስተኛ ይዞታ አርሶአደሮችም ታላቅ ዜና ነው፡፡" ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የዘመናዊ ግብርና አገልግሎት መርሃ ግብር ዩኤስ ኤ አይ ዲ ከፕሬዚደንት ኦባማ ፊድ ዘ ፊውቸር መርሃ ግብር በሚደረግለት ድጋፍ የሚያከናውነው የሁለት ዓመት የሙከራ መርሃ ግብር ነው፡፡ ዩኤስ ኤ አይ ዲ በፊድ ዘ ፊውቸር አማካኝነት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቤተሰቦች በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ እና ምርቶችን የመግዛት ፍላጎት መፍጠር እንዲችሉ እገዛ በማድረግ ላይ ነው፡፡እነዚህ ተግባራት ለገጠር ነዋሪዎች የስራ ዕድል እና ገቢ ያስገኛሉ፡፡

###